## 2. የገቢዎች ሚኒስቴር የ2014 ዓ.ም ዓመታዊ እቅድ ግብረ-መልስ

### ጥንካሬ የተለዩ ጉዳዮች

- የባለ ብዙ ዘርፍ ወጣቱ አካላዊ ብቃቱ እና ጤንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እና ውድድር የሚያደርግበት ሁኔታ መፍጠር መቻሉ፣ አረንጓዴ ልማትን ከመደገፍ አንጻር የችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ ስራ መሰራቱ፣ በተቋሙ የሚገኙ አካል ጉዳተኞችን በመለየት ድጋፍ መደረጉ፣ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ላለ እና በቫይረሱ ምክንያት ወላጅ እና አሳዳጊያቸውን ላጡ ድጋፍ መደረጉ እንዲሁም የውስጥ እና የውጪ ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ተቋሙ በ2013 በጀት ዓመት ያደረጋቸው ጥረቶች እጅግ አበረታች መሆኑን፤
- ከአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር አብዛኛው አገልግሎቶች በስታንዳርድ እና ከስታንዳርድ ባነሰ ጊዜ እየተሰጠ የቆየ ቢሆንም ይህን የአገልግሎት አሰጣጥ መፈተሽና ተገልጋዮች ያላቸውን የዕርካታ ደረጃ በማወቅ በተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በማሻሻል የተገልጋዮች ዕርካታን ማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን በቀጣይ መስራት አስፈላጊ በመሆኑ  በዚሁ መሠረት ጥናት ተካሂዶ አገልግሎት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ከመስጠት አንጻር ማሻሸሎች መኖሩን፤
- በአጠቃላይ የታክስ ማጭበርበርና እና ኮንትሮባንድን መከላከል የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነትን በላቀ ደረጃ የማረጋገጥ እና ህገወጥ ግብር ከፋዮችንና አስተላላፊዎችን ወደ ህግ ስርዓት የማምጣት ስራ ተጠናክሮ የሚሰራ በትኩረት መስኩ ስር የተቀመጡ መሆኑ እንደጥንካሬ የሚወሰድ ይሆናል፤
- በ2014 በጀት ዓመት በዋናነት ለገቢ ቀጥተኛ ወይም በተዘዋዋሪ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ያላቸው ስራዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የማስታወቅ እና ክፍያ መፈጸም፣ ኦዲት፣ ቅሬታ እና ግብር ይግባኝ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ክትትል እና ቁጥጥር፣ የታክስ ማጭበርበር እና ሀሰተኛ ደረሰኝ ቁጥጥር፣ ዕዳ አሰባሰብ እና የኤክሳይስ ታክስ ትግበራን ማጠናከር ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው ስራዎች ናቸው፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ለይ ትኩረት መስጣቱ ገቢን ከመሰብሰብ አንፃር እንደጠንካራ  ጎን ልወሰድ የሚገባ ጉዳይ ነው፤

**በጉድለት የተለዩ ጉዳዮች**

- የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት ልማትን በተመለከተ የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ስርዓት ላይ መጠነኛ ማሻሻያ እየተደረገ አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ፣ የጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ስርዓት (ECMS) ማሻሻያ ተደርጎ ወደ ትግበራ መገባቱ፣ ተገልጋዮች በአካል መምጣት ሳያስፈልጋቸው የኤሌክትሮኒክስ ስርዓትን ተጠቅመው ግብርና ታክሳቸውን እንዲያሳውቁና እንዲከፍሉ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት በስራ ላይ መዋሉ በ2013 በጀት ዓመት ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ወደ ወረቀት አልባ የአገልግሎት አሰጣጥ በመቀየር የተገልጋዮችን እንግልትና ወጪ ለመቀነስ ያደረጋቸው ጥረቶች ማሳያ ናቸው።ይላል ነገር ግን ምን ያህል ተገልጋይ በዚህ ቴክኖሎጂ እየተጠመ መሆኑን የሚያሳይ ቁጥርም ሆነ ማሳያ ነገሮችን መጥቀስ ያለ መቻሉ፤
- የባለ ብዙ ዘርፍ አካታችነት እና ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር የሴቶች የአመራር አቅምን በማሳደግ የሴቶች አመራር ድርሻን በገቢዎች ሚኒስቴር 40 በመቶ እንዲሁም በጉምሩክ ኮሚሽን 23 በመቶ መድረሱ፣ የሴት ሰራተኞች ድርሻ በገቢዎች ሚኒስቴር 54 በመቶ እንዲሁም በጉምሩክ ኮሚሽን 43 በመቶ መድረሱ፣ የህጻናት ማቆያዎች መከፈታቸው፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ሰራተኞች ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት አማራጮች መፈጠራቸው፣ አነስተኛ የስራ መደብ ላይ ያሉ ሰራተኞች የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ መደረጉ፣ጥሩ ብሆንም ነገር ግን ጉምሩክ ኮሚሺን በኩል ሴቶችን ወደ አመራር ደረጃ ማሳደግ ዝቅተኛ መሆኑንና ዝቅተኛ ገቢ ያለቸውን ሴቶች ምን ያህል ቁጥር የትምህርት እድል እንደያገኙ ድጋፍ መደረጉ የሚያሳዩ ቁጥረ ያለመኖሩ፤
- የተቋሙ የመንግሥት ተሿሚዎች፣ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ሀብትና ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ ማድረግ፣ አገልግሎት ሲያቋርጡ አገልግሎት ማቋረጥ ምዝገባ አካሂደው እንዲለቁ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የምዝገባ መረጃ ማደራጀት፣ ወቅታዊ ማድረግና ለኮሚሽኑ መላክ፣ የተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራርን ለማጠናከር ተቋማዊ ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ለተቋሙ የበላይ  አመራር ማቅረብ እና በሥነ-ምግባራቸውና ሙስና በመከላከል ረገድ ላቅ ያለ ድርሻ ላስመዘገቡ

ሠራተኞች ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ በ2014 በጀት አመቱ ጥሩ በሆንም በ2013በጀት አመት በዚህ ዘርፍ የተሰራ ስራ ያለመኖሩ፤

**በቀጣይ ትኩረት ሊደረግባቸውና ሊተገበሩ የሚገቡ ጉዳዮች**

- መስሪያ ቤቱ ለቅሬታና አቤቱታ ተገላጭ ከመሆኑ የተነሰ የቀረቡ ቅሬታዎችና አቤቱታ በተለይም አግባብነት ያላቸው ቅሬታዎች በ2013 በጀት ዓመቱ ቀርበው የተፈቱና ያልተፈቱት በቁጥር ስንት እነደሆነ በመረጃ የተደገፋ ነገር ያለመኖሩ፤ በቀጣይ ትኩረት የሚሸው ጉዳይ ነው፤
- የተቋሙ የመንግሥት ተሿሚዎች፣ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ሀብትና ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ ማድረግ፣ አገልግሎት ሲያቋርጡ አገልግሎት ማቋረጥ ምዝገባ አካሄደው እንዲለቁ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የምዝገባ መረጃ ማደራጀት፣ ወቅታዊ ማድረግና ለኮሚሽኑ መላክ፣ የተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራርን ለማጠናከር ተቋማዊ ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ለተቋሙ የበላይ  አመራር ማቅረብ እና በሥነ-ምግባራቸውና ሙስና በመከላከል ረገድ ላቅ ያለ ድርሻ ላስመዘገቡ ሠራተኞች ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ በ2014 በጀት አመቱ ጥሩ በሆንም በ2013በጀት አመት በዚህ ዘርፍ የተሰራ ስራ ያለመኖሩ፤ይህን ችግር ለመፍታት በመረጃ የተደረጃ ስራ መስራት ይኖርበታል፤
- አዲሱ የኤክሳይስ ታክስ ፖሊሲ ሀገራችን ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ከማሳደግ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽዎ አለው፡፡ በዚህ ረገድ በገቢ ድርሻ ላይ ከመቶኛ ባለመቀመጡ ድርሻው ግልፅ ያለመሆኑና በርካቶቹ እንደቅሬታ ምንጭ እየተጠቀሙ ስለሆነ ተቋሙ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥተው መሰራት አስፈላጊ መሆኑን ነው፤
- ዕቅዱ በBSC የታቀዱ ወደ መጨረሻ ያሉ የእቅዱ አካል ከላይ ካለው ናራቲቭ እቅድ ድግግሞሽ መሆኑንና BSC እቅድም ብሆን በጊዜ፤በጠንና፤በወጪ ያልተቀመጣ መሆኑን፤ በሁለቱም አንድን እቅድ ከማቀድ ይሊቅ በአንዱ መታቀድ የስፈልጋል፤